ከደሙ ንጹህ ነኝ ማለት የሚችል ጲላጦስ ብቻ ነው

## የአኝዋክ ሰማዕታት

ፀሀይዋ ልትጠልቅ ከገጠር ከተማ
ከአድማሱ ላይ ቆማ ጋምቤላና ዲማ
ደመናውም ቀልቶ ደም መስሎ ይታያል
የምድሩን ጉድ አይቶ ለግዜር አቤት ይላል

የመንግስት ወታደር በር እየሰበረ
ገበያ በትኖ ሰው እያባረረ
አጨዶው በጥይት እያነባበረ
ታድኖ ተፈጀ አኝዋክ በመንደሩ
እንደ ጭዳ ከብት ታረደ ባገሩ

ደርሶ እየፈነዳ የተቀበረው ቦንብ
ጊዜውን ጠብቆ የዘረኞች ሂሳብ
አንዱን ወገን ካንዱ ጀመረ ማዋከብ
የሞት ጥላ ወርዶ እዛ በምዕራብ
አዝመራው ታጨደ የተንኮለኞች ምናብ

ደግ ግዜ ራቀ ክፉ ግዜ ኮራ
እባብ የረጨው መርዝ ፍሬ እያፈራ
ተባብሮ እንዳልኖረ አንዱ ካንዱ ጋራ
ጎሳ ለጎሳ ፍቅር እንዳልተጋራ
በግብዞች ጥበብ በዘረኞች ሴራ
ደም ይቃባ ጀመር ሆኖ ባላጋራ

ደርሶ የሚታደግ ወገን አቅም አጥተው
ቁያቸውን ጥለው ሺ አዕላፍ ሆነው
ተሰደዱ ወጡ ሄዱ አገር ለቀው
ከጎረቤት አገር መድረሻ ጠፍትዋቸው

መሪውም አልቀረ አገር ጥሎ ፈለሰ
ህዝቡም ተበትነ ልዕልናው ፈረሰ
ዛሬ የአኝዋክ ዕጣ ዕድሉ ደረሰ
ማነሽ ባለሳምንት መርዙን የቀመሰ
አገር ሲፈርስ እንዲህ ነው እየተቀረሰ

የሰማዕታት ቀን በአኝዋኮች ህይወት
ትውልድን የሚዘልቅ የማይረሳ ዕልቂት
ሆኖ ይታሰባል ይቺ ቀን ይቺ ዕለት
የህውዚን ባለሙዋሎች የሰይጣን በረከት

ናፈቅኩት ጊዜውን እንዳው ቶሎ ደርሶ
ዘረኛው ፍርድ ቤት በዚም ግፍ ተከሶ
የጅን እንዲያገኘው ፍትህ ባገር ነግሶ
ፍትህ ባገር ነግሶ

ጃዊሳ

ተጻፈ February 2004

http://www.solidaritymovement.org/090323GenocideWatchCallsOnUN.php

## ማን ጠያቂ አለው

ምን ፍትህ ቢረገጥ ርትዕ ቢታገት

ህግ ቢጎነደል ቢረዝም ሰንሰለት

ቢገን ጭለማ ቢገዝፍ በእብሪት

አይቀር መፈንጠቁ

…….ጨረር ጮራ የንጋት

አይቀር መተካቱ

…….ብርሃነ ህሊና  ምልአት ነጻነት

…በህግ የበላይነት

….በዲሞክራሲያዊ ስርአት

ማን ጠያቂ አለው

…………የታሪክን ሂደት

April 2009

jawissa09@gmail.com